**የ20ኛው ክኔሴት ማዕከላዊ የምርጫ ኮሚቴ**

**የእስራኤል የምርጫ ሥርዓቶች**

## የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ የመረጃ ወረቀት - የክኔሴት ምርጫ

**“የበዓል (“ሞዔድ”) ቀን፣ የዲሞክራሲን ቀን እንዳንስተው። ይህ ከኛ ጋር የቆየ ዲሞክራሲ ሲሆን የማንተወው ዲሞክራሲ ነው። ነገ አንተ፣ አንቺና ሁላችንም ለክኔሴት ማን እንደሚመረጥና መንግሥት ምን ዓይነት እንደሚሆን እንወስናለን። ይህ ብልህነት የተመላበት ዲሞክራሲ ነው። ነገ በክኔሴት ማን እንደሚቀመጥ፣ በተዘዋዋሪ በመንግሥት ውስጥ ማን እንደሚቀመጥ የምንወስን ይሆናል። የዕለት አጀንዳችንን ከነገ ወዲያና በቀጣዮቹ ቀናት ማን እንደሚወስን የምንመርጠው እኛ ነን። በእስራኤል ሀገርና ኅበረተሰብ ውስጥ ምን መደረግ እንዳለበት ቁርጥ ውሳኔ የሚሰጡት ሰዎች ማን እንደሚሆኑ የምንወስነው እኛ ነን”።**

(ክቡር ሚሸኤል ሄሺን፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ
የ16ኛው ክኔሴት ማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ሊቀ መንበር)

**<u>የክኔሴት ምርጫ ዘዴ መመሪያዎች</u>**

**የመሠረታዊው ሕግ 4ኛ አንቀጽ፡ ክኔሴት ወደ ክኔሴት ለመግባት የሚደረግ የምርጫ ዘዴን ይወስናል። በመሆኑም ምርጫዎቹ የሚከተሉትን የሚያንጸባርቁ ናቸው።**

- <u>አጠቃላይነት</u> – ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የአገሪቱ ዜጋ በምርጫዎች ላይ የመሳተፍ መብት አለው።

- <u>ብሔራዊነት</u> – የምርጫዎቹን ውጤቶች ለማስላት ያስችል ዘንድ መላው እስራኤል እንደ አንድ የምርጫ ክልል ተደርጐ ይታያል።

- <u>ቀጥተኛነት</u> – የምርጫዎቹ ውጤቶች የሚወሰኑት በቀጥታ ድምጽ አሰጣጥ መሠረት መራጩ በሚሰጠው ድምጽ መሠረት ነው። ማለትም ያለሦስተኛ/መሐል መራጭና ያለውክልና ነው።

- <u>እኩል የሆኑ ናቸው</u> – ከምርጫው እኩልነት በተጨማሪ እያንዳንዱ ለክኔሴት የሚወዳደረው ፓርቲ ያለውን የመመረጥ ዕድል የመጠበቅ ግዴታም አለ።

- <u>ምስጢራዊ</u> – የድምጽ አሰጣጡ ምስጢራዊ የሆነበት ምክንያት መራጩ በዝንባሌውና በአመለካከቱ ሊመርጥ ይችል ዘንድ እና ተገቢ ያልሆኑ ጫናዎችና ግፊቶች እንዳይደረጉበት በማለት ነው።

- <u>ተመጣጣኝነት</u> – በክኔሴት ውስጥ የ“ማንዳት” ክፍፍል የሚደረገው እያንዳንዱ ፓርቲ ባገኘው ድምጽ መሠረት ነው።

# የክኔሴት ምርጫዎች የሚካሄዱት አዳር 26 ቀን 5775 ዓ.ዓ. ወይም ማርች 17 ቀን 2015 ዓ.ም. ነው።

## የመምረጥ መብት



የመምረጥ መብት ሕገ መንግሥታዊ መብት ሲሆን በመሠረታዊው የክኔሴት ሕግ በአንቀጽ 5 ተደንግጓል። ይህ መብት የሚሰጠው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚያሟላ ለሁሉም የእስራኤል ዜጋ ነው።

በክኔሴት ምርጫ ቀን ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ (በ4.4.97 ወይም ከዚያ በፊት የተወለደ)

በመራጮች መዝገብ ላይ የእስራኤል ዜጋ ሆኖ የተመዘገበና በሕዝብ መዝገብ ከሽቫት 2 ቀን 5775 ዓ.ዓ. (ከጃኑዋሪ 22 ቀን 2015 ዓ.ም.) በፊት ተመዝግቦ የሚገኝ

በእስራኤል አገር ኗሪነት ተመዝግቦ የነበረና ስሙና አድራሻው በእስራኤል ውስጥ በሕዝብ መዝገብ ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኝ ከሆነ


የመራጮች መዝገብ በኢንቴርኔት ድረ ገጽ ላይ የሚቀርብ ሲሆን ይህም የምርጫ ቦታን ለማወቅ እንዲያስችል ተብሎ ነው። መዝገቡ www. bechirot gov.il በተባለው የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ ላይ "איתור קלפי" ከሚለው በታች ይቀርባል።

## ድምጽ የሚሰጠው የት ነው?

እያንዳንዱ መራጭ ድምጽ መስጠት የሚችለው የራሱን ስም በያዘ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ ሲሆን መምረጥ የሚፈቀድለትም በዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው። መራጭን ከምርጫ ጣቢያ ጋር እንዲያያዝ የተደረገበት መርህ የምርጫው አመራር ትክክለኛና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ታስቦ ነው።

መራጩ የትኛው የድምጽ መስጫ ቦታ እንደተመደበ የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ በሆነው በwww.bechirot.gov.il ማጣራት ይችላል። በተጨማሪም ለእያንዳንዱ መራጭ በመኖሪያ አድራሻው መሠረት የትኛው የድምጽ መስጫ ቦታ እንደተመደበ የሚገልጽ ወረቀት ተልኮለታል። እንደዚሁም ከምርጫው ቀን በፊት ቴሌፎናዊ የማብራሪያ ጣቢያ ("ሞኬድ") ይከፈታል።

**ከድምጽ መስጫው ቦታ ጋር ያለመያያዝ የማይመለከታቸው** - የክኔሴት ምርጫ ሕግ የማይመለከታቸው ብሎ የሚወስናቸው በቁጥር የተወሰኑ አሉ። መራጩ ወደተመደበበት ድምጽ መስጫ ጣቢያ እንዳይደርስ የሚያደርገው እክል ካለ፡- ለምሳሌ ያህል ከአካላዊ ሁኔታ የተነሣ እንቅስቃሴው ውሱን የሆነ ሰው፣ ሆስፒታል ውስጥ በሕክምና ላይ የሚገኝ፣ በማረሚያ ቤት የሚገኝ የሕግ ታራሚ፣ ወታደር እና በዲፕሎማሲ መስክ ውጭ አገር የሚሠራ። በእነዚህ ሁኔታዎች ድምጽ መስጠት የሚካሄደው ውጫዊ በሆኑ (ድርብ በሆኑ) ፖስታዎች አማካይነት ነው የሚደረገው።




– **<u>የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ሰዎች የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ሰዎች ተብለው በተዘጋጁ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጽ መስጠት ይችላሉ።</u>**

- **<u>መራጩ ከድምጽ መስጫ ጣቢያ ፀሐፊ ፊት ቀርቦ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደማይችል ካስታወቀ (ይህን</u>**

የሚያደርገው አካለ ስንኩልነቱ በዓይን ተለይቶ ሊታይ የማይችል ከሆነ ነው) በምርጫ ጣቢያው ውስጥ እንዲመርጥ ፈቃድ ይሰጠዋል።

ልብ ማድረግ ያለብን ነገር - የአካላዊ እንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ሰዎች ድርብ በሆኑ ፖስታዎች አማካይነት ተደራሽ በሆኑ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምጽ እንዲሰጡ የሚደረጉት የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን ሰዎች እንዲቀልላቸው በማሰብ ነው። የአካል እንቅስቃሴ ችግር ሳይኖር "ችግር አለብኝ" ብሎ መራጩ ባልተመዘገበበት ድምጽ መስጫ ቦታ ድምጽ መስጠት ተደራሽ በሆኑ ድምጽ መስጫ ቦታዎች ከፍተኛ ጭንቅንቅ እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህም የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ድምጽ የመስጠት ሂደት ያስተጓጉላል። በመሆኑም የአካል እንቅስቃሴ ችግር ሳይኖርበት "ችግር አለብኝ" ብሎ የተናገረ የሚደርስበት ቅጣት የግማሽ ዓመት እስራት ወይም የገንዘብ ቅጣት ነው። ከላይ በተጠቀሱት ቴሌፎናዊ የመረጃ ቢሮዎችና በማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ አማካይነት ተደራሽ የሆኑ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን ማጣራት ይቻላል።



## የድምጽ መስጫው ኮሚቴ

የድምጽ መስጫውን ቦታ ሆነ የድምጽ አሰጣጡን ሥርዓት የሚያስተባብረው የድምጽ መስጫ ኮሚቴ ነው። ይህ ኮሚቴ የሚዋቀረው ከድምጽ መስጫ ኮሚቴ ሲሆን ይህም የሚይዘው የክኔሴት አንጃዎች ተወካዮችን ሆኖ የኮሚቴው ጸሐፊ በድምጽ መስጫው ቦታ የማዕከላዊ  ምርጫ  ኮሚቴ ተወካይ ይሆናል ማለት ነው። ለኮሚቴው አባላትና ለጸሐፊው በሕጉ የተደነገጉ የተለያዩ ሥራዎች አሉ። ከእነሱም መካከል፡- የድምጽ መስጫውን ቦታ መክፈት፣ መራጮች ድምጽ ለመስጠት በሚመጡበት ጊዜ ማንነታቸውን መለየት፣ ድምጽ የሰጡትን ሰዎች ምልክት ማድረግና ከመዝገቡ መፋቅ፣ እንደዚሁም የድምጽ መስጫውን ቦታ መዝጋትና የተሰጡትን ድምጾች መቁጠር ናቸው።

## የምርጫው  ቀን

የምርጫው ቀን ሥራ የማይሠራበት ቀን ነው። ቢሆንም ግን የሕዝብ ማመላለሻዎች እና ሌሎች የማዕከላዊ  ምርጫ ኮሚቴ የወሰናቸው የሕዝብ አገልግሎቶች (ምግብ ቤቶች፣ ቴያትር ቤቶችና ሲኒማ ቤቶች፣ የውሃ ፋብሪካዎችና የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ሆስፒታሎች፣ ሕይወት አድን ድርጅቶች፣ ወዘተ.) በተለምዶው ዓይነት ይሠራሉ።

በምርጫው ቀን የድምጽ መስጫ ቦታዎች ከጧቱ 7 ሰዓት እስከ ምሽቱ 10 ክፍት ናቸው። በትናንሽ መንደሮች ድምጽ የሚሰጠው ከጧቱ 8 እስከ ምሽቱ 8 ሰዓት ድረስ ነው። በሆስፒታሎች፣ በማረሚያ ቤቶች እና በጊዜያዊ ማገቻ ቦታዎች ድምጽ የሚሰጠው እንደዚሁ ነው።

የድምጽ መስጫዎቹ ቦታዎች ከላይ በተጠቀሱት ሰዓቶች ይዘጋሉ። በሮቹ ሳይዘጉ ወደ ድምጽ መስጫው ቦታ የመጣና ድምጽ ያልሰጠ ሰው - የድምጽ መስጫው ጣቢያ የመዝጊያ ሰዓት ያለፈ ቢሆንም ድምጽ መስጠት ይችላል።

## በድርብ ፖስታ አማካይነት ድምጽ መስጠት

እንደተጠቀሰው በድርብ ፖስታ አማካይነት ድምጽ የሚሰጡ ሰዎች አሉ። በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ ድምጽ ሰጪው በድምጽ መስጫው ወረቀት ላይ ዝርዝሮች (ስም፣ የመታወቂያ ቁጥር፣ አድራሻ) በመጨመር ወደ መደበኛው የድምጽ መስጫ ፖስታ ውስጥ ይከታል። ይህንን ፖስታ በሌላ ፖስታ ውስጥ ይከተዋል። ይህ ፖስታ በድምጽ መስጫው ሳጥን ውስጥ ይከተትና ከሌሎች ድምጽ ከተሰጠባቸው ወረቀቶች ጋር ይቀላቀላል። በምርጫው ቀን መጨረሻ ድርብ ፖስታዎቹ ይሰበሰቡና አንድ ላይ ይጠራቀማሉ። ድርብ ፖስታዎቹ ክኔሴት ውስጥ ወደሚገኘው

የማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ቢሮ ይላካሉ። ከዚያም ድርብ ፖስታዎቹና በላያቸው ላይ ዝርዝሩን የጻፉት ሰዎች ማንነት ይመረመራል። ኮሚቴው በድርብ ፖስታው ድምጽ የሰጠው ግለሰብ በተመዘገበበት ድምጽ መስጫ ቦታ ሌላ ድምጽ እንዳልሰጠ ይመረምራል። ይህም ድርብ ድምጽ መስጠትን ለመቆጣጠር በማለት ነው። ከዚህ ምርመራ በኋላ ውስጣዊ ፖስታዎች ይሰበሰቡና ያለምንም መለያ ወደ ማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴዎች ቢሮ ይተላለፋሉ። እነዚህ ኮሚቴዎች ከመደበኛው ድምጽ መስጫ ኮሚቴዎች ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ እነዚህ ኮሚቴዎች በፖስታዎቹ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይቆጥራሉ።

***እስራኤል ውስጥ ለክኔሴት የሚደረጉት ምርጫዎች በፓርቲው ለሚቀርቡ ዕጩ ፓርቲዎች የሚደረግ ምርጫ ነው።*** *እያንዳንዱ ፓርቲ ፊደል ወይም ፊደላት እንደዚሁም መጠሪያ አለው። የፓርቲው ፊደላትና መጠሪያው በድምጽ መስጫው ወረቀት ላይ ይታተማሉ። በምርጫው ጊዜ ለመራጩ የሚቀርቡት ሁሉም የፓርቲዎቹ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ሲሆኑ መራጩም እሱ ድምጽ ለመስጠት ለሚፈልገው ፓርቲ የሚስማማ ድምጽ መስጫ ወረቀት ይመርጣል። የፓርቲዎች መጠሪያ እና ፊደላቶቻቸው በጋዜጣ ላይ የሚታተሙ ሲሆን በማዕከላዊ ምርጫ ኮሚቴ ድረ ገጽ ላይም ይቀርባሉ።*

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች

ሀ. መራጩ ለአስመራጩ ኮሚቴ ፀሐፊ ራሱን ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ ያስተዋውቃል።

- የባለቤቱን ፎቶ በያዘ መታወቂያ ወረቀት አማካይነት
- ቀኑ ያላለፈበትና ፎቶ የያዘ የእስራኤል ፓስፖርት
- ቀኑ ያላለፈበትና ፎቶ የያዘ የእስራኤል መንጃ ፈቃድ



(ለ) መራጩ ስሙ በመራጮች መዝገብ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ "የ20ኛው ክኔሴት ምርጫ" ተብሎ የተጻፈበትና ሰማያዊ ቀለም ያለው የምርጫ ፖስታ ይቀበላል።

(ሐ) መራጩ ወደ ድምጽ መስጫው የተከለለ ቦታ ውስጥ **ብቻውን** ይገባል። በበሽታና ሌላ አካላዊ ችግር የተነሣ በምርጫው ቦታ ውስጥ እንቅስቃሴ ሊያደርግ የማይችል ሰው በድምጽ አሰጣጥ ሂደት የሚረዳውን ሰው ለማምጣት ይፈቀድለታል። ነገር ግን የሚረዳው ግለሰብ የአዛውንት ተጧሪዎች መኖሪያ ወይም ማንኛውም እርዳታ የሚያሻው ድምጽ ሰጪ በሚኖርበት ተቋም ውስጥ የሚሠራ ሠራተኛ ወይም ሥራ አስኪያጅ መሆን የለበትም። ይህን እርዳታ የሚሰጠው ሰው በምርጫው ቀን ከ2 በላይ ሰዎችን ለማጀብ አይችልም። መራጩ ከፊት ለፊቱ ለክኔሴት ዕጩ የሆኑ ፓርቲዎች ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቀምጠው ያገኛል። እንደዚሁም በድምጽ መስጫው ውስጥ ነጭና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችም ይገኛሉ።

(መ) ድምጽ ሰጪው እሱ ሊመርጠው የሚፈልገው ፓርቲ ስምና ፊደል ያለበት **አንድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ብቻ** ይመርጣል። ከዚያም ያንን ወረቀት በክኔሴት ምርጫ ፖስታ ውስጥ ይከተዋል። መራጩ ፖስታውን መዝጋት አለበት። መራጩ ከፈለገ በነጭና ባዶ የድምጽ መስጫ ወረቀትም መጠቀም ይቻላል። በዚያም ወረቀት ላይ የሚመርጠውን ፓርቲ ፊደልና ስም ይጽፋል (መጻፍ የሚችለው በዕብራይስጥ ወይም በዓረብኛ ብቻ ነው)።



**ማሳሰቢያ - የፓርቲው ፊደል ወይም ስም ያልተጻፈባቸው ነጭ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ውድቅ የሆኑ የሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ናቸው። እነዚህ ወረቀቶች የማይቆጠሩ ሲሆን የሚጨመሩትም ውድቅ ከሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ ነው።**

(ሠ) ወደምርጫው ፖስታ አንድ የድምጽ መስጫ ወረቀት ብቻ መከተት ያስፈልጋል። በአንድ ፖስታ ውስጥ ሁለት የአንድ ፓርቲ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቢገኙ ድምጹ አይሰረዝም (ነገር ግን አንድ ወረቀት ብቻ ነው ከግምት የሚገባው)። ነገር ግን በፖስታው ውስጥ **ከ2 በላይ** የአንድ ፓርቲ ድምጽ ወረቀቶች ወይም የተለያዩ ፓርቲዎች **ድምጽ መስጫ ወረቀቶች** ቢገኙ **ድምጹ ይሰረዛል።**

**(ረ)** መራጩ ከተከለለው ቦታ ውስጥ በመውጣትና በእጁ የታሸገውን ፖስታ በመያዝ ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን በመቅረብ የኮሚቴው አባላት እያዩት ፖስታውን ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን በገዛ እጁ ይከትታል።

## የምርጫ ውጤቶች

1. ከተጣሩት ድምጾች ክፍፍል ቢያንስ 3.25%% የተቀበሉ ማንኛቸውም ፓርቲዎች በማንዳት (מנדט) ክፍፍል ላይ ይሳተፋሉ።
2. በክፍፍሉ ላይ የሚሳተፉት ፓርቲዎች የተጣሩ ድምጾች ለ120 የሚካፈል ሲሆን በማካፈል የሚገኘው ውጤት ቁጥር “መለኪያ” (מודד) ይሆናል።
3. ሁሉም ፓርቲ የሚያመጣው ድምጽ በመለኪያው ውጤት ከተከፋፈለ በኋላ ተገቢውን የማንዳት (מנדט) ቁጥር ያሸንፋል
4. ቀጥሎም ትርፍ ድምጾች በሕጉ መሠረት ይከፋፈላሉ። (ይህም "עופר – באדר" ተብሎ በሚታወቀው ዘዴ መሠረት ነው)።


የመጀመሪያው (ኦሪጂናል) የዕብራይስጥ ጽሑፍ
**የ20ኛው ክኔሴት**
**ማዕከላዊ የምርጫ ኮሚቴ**
www.bechirot.gov.il

“የ20ኛው ክኔሴት ምርጫ” መረጃ ወረቀት የአማርኛ ትርጉም
ለአዲስ ገቢዎች አገልግሎት ተብሎ የተዘጋጀ
**የአዲስ ገቢዎች ማስተናገጃ መሥሪያ ቤት፣ የኅትመት ክፍል**
www.klita.gov.il


**ኢየሩሳሌም 2015 – መብቱ የተጠበቀ ነው – ©**